

# ስለ አለም አቀፍ ጥበቃ በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ጥገኝነት ጥያቄ/አለም አቀፍ ጥበቃ የመጠየቅ መብት ያላቸው እነማን ናቸው?

የግሪክ አገር መንግስት ከሦስተኛ አገር ዜጎች ወይም ዜግነት አልባ ለሆኑ እንዲሁም በብሄራቸው፣ ሃይማኖታቸው፣ ዜግኔታቸው ወይም የተለየ ማህበራዊ ቡድን ውስጥ በመሳተፋቸው እንዲሁም ደግሞ በፖለቲካዊ አቋማቸው ምክኒያት ጥቃት ሊደርስባቸው ለሚችል ግለሰቦች ጥገኝነት፤ የአለም አቀፍ እና የፖለቲካ  ጥበቃ በመስጠት ከጥቃቱ እንዲጠበቁ ይረዳል። በትውልድ አገራቸው ወይም ቀደም ሲል በሚኖሩበት ቦታ ለከፍተኛ ጉዳት የመዳረግ አደጋ  በተለይም የሞት ቅጣት ወይም ግድያ ፣ ስቃይ፣ ወይም ኢሰብአዊ ለሆኑ የክብር ጥሰቶች የተጋለጡ ከሆነ፣ በአለም አቀፍ ወይም በእርስ በርስ ግጭቶች ምክኒያት ሕይወታቸው ወይም ሙሉ አካላቸውን የሚያሰናክል ጉዳት ሊከሰት ይችላል የሚል ፍራቻ ካለ የግሪክ መንግስት ጥበቃ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ሌሎች መጠቀስ ያለባቸው ምክንያቶች ናቸው።

## የጥገኝነት ጥያቄ እንዴት ማቅረብ እችላለው?

ማንነት ማረጋገጫ እና መቀበያ ማዕከል እያሉ አለም አቀፍ ጥበቃ/ጥገኝነት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ይህን ፍላጎትዎን

ከገለጹ በኋላ የማዕከሉ ሰራተኞች ማመልከቻ ማስገባት ይችሉ ዘንድ ለሚመለከተው የጥገኝነት አገልግሎት ቅርንጫፍ ያስተላልፋል።

አሊያም የጥገኝነት ጥያቄዎትን ምዝገባ በሚከተለው ድረ-ገፅ
በመጠቀም በኤሌክትሮኒክስ መልክ ማከናወን
ይችላሉ: https://apps.migration.gov.gr/selfregistration/login

**የጥገኝነት ጥያቄ ለማቅረብ መክፈል ይኖርብኛል?**

መክፈል አይኖርበትም። የአለም አቀፍ ጥገኝነት ሂደት የሚከናወነው ያለ ገንዘብ ክፍያ በነፃ ነው።

**ለባለቤቴና ለልጆቼ የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ እችላለው?**

የቤተሰብዎ አባላት አብረዎት ግሪክ አገር የሚገኙ ከሆነና ማመልከቻውን ማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ አዎ ማድረግ ይችላሉ።

**ጉዳዬን የሚመረምረው የመ\ቤቱ ሰራተኛ የጥገኝነት ጥያቄዬ ውጤት አወንታዊ ወይም አሉታዊ ውሳኔ እንዲሆን የሚወስነው እንዴት ነው?**

ግላዊ ቃለ-ምልልስዎን ሲያከናውኑ የተናገሩትን፣ የጥገኝነት ጥያቄዎን ሲያቀርቡ የሰጡትን የማረጋገጫ መረጃ ወይም ሰነዶች፣ አገርዎን የሚመለከቱ መረጃዎችንና በመ/ቤቱ አስተዳደር ያለው ፋይልዎ ውስጥ የሚገኙትን መረጃዎች በአጠቃላይ በማሰባሰብና ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዳዮ መርማሪ ላቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ውሳኔ ያወጣል።

**የጥገኝነት ጥያቄ አቅርቤ ውሳኔውን በመጠባበቅ ላይ እያለሁ መጓዝ እችላለው?**

እንደ አለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂ ከግሪክ አገር ውጪ መጓዝ **አይችሉም።** ወደ ሌላ አገር መጓዝ የሚችሉት በተለየ ከባድ የሰብአዊ ምክንያቶች ብቻ ነው። ሌላ አገር መገኘት ሊኖርብዎ የሚያስችል አንዱ ምክኒያት ሊሆን የሚችለው የተረጋገጠ ከባድ የጤና ችግር ካለ ነው። የጉዞ ሰነድ ለማግኘት ለመ/ቤቱ ማመልከቻ ማቅርብ ይኖርቦታል። ለመ/ቤቱ ሳያሳውቁ አገሪቱን ለቀው ከተጓዙ ጉዳይዎ ውድቅ ይደረጋል።

### ለኢንተርቪዬ አስተርጓሚ ማምጣት ይኖርብኛል? እንግሊዘኛ ቋንቃ የማላውቅ ከሆነ ምን ሊሆን ይችላል?

ከመ/ቤቱ ጋር ለመግባባት በሚያስፈልግበት ግዜ የእርስዎን ቋንቋ የሚናገር ወይም እርስዎ የሚረዱትን ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ አስተርጓሚ የጥገኝነት መ/ቤቱ ያቀርባል።

### ያቀረብኩት የጥገኝነት ጥያቄ ስለሚገኝበት ሂደት እንዴት ማወቅ እችላለው?

በስልክ የጉዳይዎን መረጃ ስለማንሰጥ ጉዳይዎ በምን ሂደት እንደሚገኝ ማወቅ ከፈልጉ በአካል እርስዎ ወይም ተወካይ ጠበቃዎ ወደ መ/ቤቱ ቀርበው መጠየቅ ይኖርብዎታል። ሆኖም ግን በቀን በቀን ወደ መ/ቤቱ ብዙ ተስተናጋጆች ስለሚመጡ የጥገኝነት ጠያቂ ካርድዎ(ΔΑΔΠ) ሊያበቃ ሲልና ለማሳደስ ሲመጡ ጉዳይዎ ስለሚገኝበት ሂደት በተመልከተም ይነገርዎታል።

### በህገወጥ/ተገቢ ባልሆነ መልኩ ግሪክ አገር የምገኝ ብሆንም እንኳ የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ እችላለው?

ምንም እንኳ ግሪክ አገር በህገ ወጥ ወይም ተገቢ ባልሆነ መልኩ የገቡ ቢሆንም ይህ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎን ምርመራም ሆነ የጉዳይዎ ሂደት ሊስተጓጓል አይችልም። ነገር ግን ግሪክ አገር ውስጥ

በገቡ በአጭር የግዜ ገደብ ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄዎን ማቅረብ ይኖርብዎታል። ግሪክ አገር በህገ ወጥ የገቡ ከሆነ ማንነት በማረጋገጫ እና በመቀበያ ማዕከል ውስጥ የመቀመጥ ግዴታ ይኖርብዎታል። በዚህ መልኩ በሚኖሩበት ማዕከል ውስጥ ለሚገኘው ገልለተኛ የጥገኝነት አገልግሎት መስጫ አካል የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄዎን ማቅረብ ይችላሉ።

### 👉 ለአቅመ አዳም ያልደረስኩ ከሆነ ጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ እችላለሁ?

አዎ። ከአስራ አምስት አመት በታች (15) ከሆኑ ከሆነ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄዎን ማቅረብ የሚችለው ወላጅዎ ወይም እርስዎን ለመንከባከብ ሃላፊነቱን የወሰደ አንድ ለአቅመ አዳም/ሄዋን የደረሰ ግለሰብ መሆን አለበት። አጃቢ የሌለዎ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ከሆነ ከመንግስት የተመደበልዎ ተንከባካቢዎ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻውን ሊያቀርብልዎ ይችላል። እንድሜዎ ከአስራ አምስት አመት (15) በላይ ከሆነ ማመልከቻዎን በግልዎ ማቅረብ ይችላሉ። አጃቢ የሌልዎ ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ከሆነ የሚመልከተው ባለስልጣን ሊንከባከብዎና በመቀበያ ማዕከል እንዲቆዩ እንዲሁም አለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ እንዲያቀርቡ የሚረዳዎ ተንከባካቢ ይመድብልዎታል።

### 👉 ኢንተርሺዬ በማደረግበት ሰዓት ሊረዳኝ የሚችል ሰው አብሮኝ መገኘት ይችላል?

በኢንተርቪዎ ቀን ተወካይ ጠበቃ፣ ዶክተር የሶሻል ወርከር እና የስነ ልቦና ዶክተር ይዘው መቅረብ ይችላሉ።

**👉 የጥገኝነት ጥያቄዬን ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ እያለሁ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እችላለው?**

አዎን ይችላሉ። የጥገኝነት ጥያቄዎን ሲያቀርቡ የመድኃኒት እና የሆስፒታል አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ (Π.Α.Α.Υ.Π.Α.) የተሰኘውን ለውጭ አገር ዜጋ የሚሰጥ ግዚያዊ የመድህን እና የጤና አገልግሎት ቁጥር ይሰጥዎታል።

**👉 የጥገኝነት ውሳኔዬን ከወሰድኩ በኃላ(እና ጥያቄዬ ተቀባይነት ካገኘ) ወደ ሌላ ሀገር መጓዝ እችላለው?**

የፖለቲካ ጥገኝነት ውሳኔ ከወሰዱ የጉዞ ሰነድ(TDV) እንዲሰጥዎ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ነገር ግን ወደ አገርዎ መጓዝ አይችሉም። ድጋፋዊ ጥበቃ ከተሰጥዎ በተመሳሳይ የጉዞ ሰነድ እንዲሰጥዎ ማመልከት ይችላሉ ሆኖም ያቀረቡትን ማመልከቻ የጥገኝነት መ/ቤቱ የሚቀበለው ከአገርዎ ባለስልጣን የአገርዎን ብሔራዊ ፓስፖርት ማውጣት የማይችሉበት ምክኒያት አለ ብሎ ካመነ ነው።

**👉 የጥገኝነት ጥያቄዬን ማመልከቻ እና ኢንተርቪ በማደርግበት ግዜ የምሰጠው ግላዊ መረጃ ደህንነቱ የተጠበቀ ይሆናል?**

አዎ የተጠበቀ ይሆናል። መረጃዎን በሚሰጡበት ግዜ በቦታው የሚገኙ ግለሰቦች መረጃዎን በሚስጥራዊ መልኩ የመያዝ ግዴታ አለባቸው። የጥገኝነት መ/ቤቱ የአቀረቡትን የጥገኝነት ጥያቄ በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ ወደ አገርዎ ባለስልጣን አያስተላልፍም። ግሪክ አገር ለሚገኙ ለሌሎች መ/ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ የሰጡትን መረጃ መ/ቤታችን ይፋ ሊያደርግ ይችላል።

**👉 ግሪክ አገር ስላለው የጥገኝነት ጥያቄ ህግ በተመለከተ የት ማግኘት እችላለው።**

የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ህግ 4686/2020, 4636/2019, 4825/2021 በተመለከተ በግሪክኛ ቋንቋ በጥገኝነት መ/ቤት ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

### 👉 መብቶችን በተመለከተ የፖለቲካ ጥገኝነት ጥበቃ ያገኘና ጥገኝነት የጠየቀ ምን ልዩነቶች አላቸው?

የጥገኝነት ጠያቂ ማለት የአለም አቀፍ ጥበቃ ጠያቂ ካርድ የተረከበ ሲሆን በዚህ ካርድም በአገሪቷ በህጋዊ መልኩ የመኖር መብት የሚያገኝ ሲሆን የጠየቀው የጥገኝነት ጥያቄ ውሳኔ እስኪወጣ ድረስ አስፈላጊ ጉዳዮችን ለማከናወን የሚያስችለው ይሆናል። የአለም አቀፍ ጥበቃ ባለመብቶች እና የመኖርያ ፍቃድ ያገኙ፣ የግሪክ ዜጎች የሚገቧቸውን አይነት መብቶች በተመሳሳይ መልኩ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል።

### 👉 ያቀረብኩት የጥገኝነት ማመልከቻ ውድቅ ከሆነ ምን ይሆናል?

የተረከቡትን የውድቅ ውሳኔ በገለልተኛ የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን በሁለተኛ ደረጃ እንዲሰረዝ በነፃ መጠየቅ ይችላሉ። ይህን የውድቅ ውሳኔ ለመሰረዝ በተሰጠዎ የውሳኔ ወረቀት ላይ በሚፅፈው የግዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝዎን ማስገባት ይኖርቦታል። ከላይ የተጠቀሰውን የይግባኝ ሂደት ለማከናወን ነፃ የህግ ባለሞያ ማግኘት ይችላሉ። የአለም አቀፍ ጥበቃ በድጋሚ እንዲሰጠዎ ያቀረቡት የይግባኝ ጥያቄ በመጨረሻ ውድቅ ከሆነ ሀገሪቷን ለቀው እንዲሄዱ የሚያዝ ህግ ተግባራዊ ይሆናል።

### 👉 ያቀረብኩት የጥገኝነት ጥያቄ የምርመራ ሂደት የመጨረሻው ውሳኔ እስኪወጣ ስንት ግዜ ይወስዳል?

የጉዳይዎን አይነት ግምት ውስጥ በማስገባት የጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ በአጠቃላይ ከሃያ (20) ቀን እስከ ስድስት (6) ወር ይወስዳል።